ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ
በ ነሐሴ 20 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## ያልተዘመረላቸው ፤ ያልተለቀሰላቸው!

ኢትዮጵያ በተፈራራቂ የታሪክ ምዕራፎች ከባድና ቀላል ችግሮችን አልፋ አሁን ካለችበት አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ደርሳለች። መቸ እንደሚሆን ባይታወቅም የወቅቱንም ችግሯን ያለጥርጥር ታልፋዋለች። ተወጣዋለች። ከችግሯ የሚያወጣት ኢትዮጵያዊ ኃይል ካለ ! መኖሩ ደግሞ የሚካድ አይደለም ። አሁን ግን ፤ ከገባችበት ምስቅልቅል ሊያወጣት የሚችል ኃይል እንደሌላት ተቆጥሯል። ያ ኢትዮጵያዊ ኃይል ግን አለ ! በተደጋጋሚ ጊዜያት፤ በህልውናዋ ላይ የተጋረጡባትን ፈታኝ ጥያቄዎች ሁሉ ፤ በዘዴም ይሁን በኃይል የፈቱላት ልጆች ነበሯት። አሁን እንደ እነዚህ ያሉ ባለ ራዕይ ዜጎች ይኑሩ፤ አይኑሩ በዕርግጠኝነት መናገር ከማትችልበት ደረጃ ደርሳለች በማለት አስተያየት ለመስጠት የሚቃጡ ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል። ሀቁ ግን ኢትዮጵያን ከገባችበት አዘቅት ሊያወጧት የሚችሉ ቁርጠኛ ልጆች ነበሯት፤ ዛሬም አሏት !

ዛሬም እንደ ትላንቱ፤ ሀገሪቱ፤ አቅጣጫው ጠፍቶባት፤ በዙሪያ ጥምጥም እምቧለሌ ትሽከረከራለች። ዜጎቿም፤ መላ-ቅጡ ጠፍቶባቸው ፤ ከገቡበት ማጥ ለመውጣት የሚያስችላቸውን መፍትሔ ማግኘት እንደተሳናቸው በተደጋጋሚ ተመስክሮባቸዋል ። ይህም በመሆኑ ፤ በየቦታው መንደርተኛ አጉራ-ዘለል ነውጠኞች እየተነሱ ሠላምና ፀጥታ ነስተዋቸዋል። ይኸ ሁኔታ ለግማሽ ምዕተ- ዐመት ቀጥሏል። በዕርግጥ ፤ ኢትዮጵያን ከወቅቱ አስቸጋሪ ሁኔታ የሚያወጣት፤ እንደ ስድሳ-ስድስቱ ጀግና ትውልድ ያስፈልጋታል። ዛሬ፤ ጀግና እየተሰዋ፤ ጀግና ባለመተካቱ ምክንያት፤ የጀግኖች ክፍተት ተፈጥሯል !

ትላንት ፤የሀገሩን ችግር የተገነዘበው ፤ ያ ሀገር -ወዳድ ትውልድ፤ ባለ ራዕይ ነበረ። ያልተዘመረላቸውንና ያልተለቀሰላቸውን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠማዕታት ወጣቶችን ገብሮላታል። ፍቅሩን ፤

በመሥዋዕቱ ገልጾላታል። ለሀገር ፍቅር፤ ከሕይወት የበለጠ ዋጋ የሚከፈል ቢሆን ኖሮ፤ ሀገራችን በተደጋጋሚ የሚሰውሏት ጀግኖች ነበሯት ። ለኢትዮጵያ ሲባል ፤ደግሞ ደጋግሞ ከመሰዋት የበለጠ፤ ምን ዘለዓለማዊ ደስታና ክብር ሊገኝ ይችላል ? ያንን ደስታና ክብር ለማግኘት የተዘጋጁ ቆራጥ አባላትና ዜጎች ዛሬም ጨርሰው አልከሰሙም ። አሁን የሚጠበቅባቸው ግን ፤ የሀገር አለኝታ ለመሆን የሚያስችላቸውን አቅም ለመፍጠር ቁመናቸውን በገሃድ ማሳየት ብቻ ነው። አቅም ያላቸው መሆኑን ማረጋገጫው ደግሞ፤ አሁን የተዛባውን የኃይል ሚዛን ማስተካከል ሲቻል ነው። ተወደደም ተጠላ፤ የሰከነ ፖለቲካን ለመጫወት፤ የኃይል ሚዛኑ፤ በሀገር አንድነትና በሕዝብ ነፃነት ላይ ያተኮረው ትግል፤ በአስተማማኝ ደረጃ መገኘቱ ሊረጋገጥ ይገባል። አብዛኛዎቹ ድርጅቶች፤ የውሃ ላይ ኩበት ሆነው ይንሳፈፋሉ። መልኀቁ ጠፍቶባቸዋል።

በሌላ አገላለፅ፤ የሕዝብ ፖለቲካ ትግል ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው፤ የኃይል ሚዛኑ ለኢትዮጵያ አንድነት በሚታገለው ጎራ እጅ ሲገባ ብቻ ነው። በግለ ሰብና ሕዝብ መብትና ነፃነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዕት ፤ ዘላቂና አስተማማኝ መሆኑ እስከታመነበት ድረስ፤ ሰው፤ ስብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ ፤የማይገሰስ፤ የማይደፈር፤ የማይቀነስና የማይሸራረፍ ምልዑ መብትና ነፃነቱ ይከበርለታል ተብሎ ይታመናል። አሁን ያለው በዘርና ቋንቋ ላይ የተመሰረተው የኢሕዴግ ፌዴሬሽን ግን የዚኽ ተፃራሪ ነው ። ሀገር አፍራሽና ሕዝብ በታኝ ነው። ይኽን ሀገር አፍራሽና ሕዝብ በታኝ አገዛዝ የህግ ሽፋን እንዲኖረው ለማድረግ፤ ወያኔና ኦነግ ፤በኤርትራ ውስጥ ሳህል በረሀ ላይ ያረቀቁት " ሕገመንግሥት " ነው። ይኽ መርዛማ ሰነድ ፤ ላንዴና ለሁልጊዜው ከምድረ-ኢትዮጵያ መወገድ አለበት። የዚኽ ሠነድ መወገድ፤ ሀገሪቱ ሠላምና ፀጥታ እንድታገኝ በር ይከፍታል ። መከፋፈልንና መገንጣጠልን ፤ በህግ የደነገገ ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ እያለ፤ የሀገር አንድነትና የዜጎች ነጻነት ይጠበቃል ብሎ ማሰብ፤ ራስን ከአውሬዎች ጋር ለመኖር የስምምነት ውል እንደመፈራረም ይቆጠራል ።

በተውስ ቅርስና ውርስ የሚኮራ ኅብረተሰብ ፤ የራሱን ቅርስ መፍጠር እንደማይችል ሁሉ፤ ከኤርትራ በረሀ የተረቀቀ ሠነድ፤ የሀገራችን ቅርስ ሆኖ ሊቆይ አይችልም። አይገባውምም። ትላንት የኢትዮጵያ አካል የነበረችው ኤርትራ፤ ዛሬ የራሷን ኅልውና ፈጥራ አንድነቷን ጠብቃ እየኖረች፤ ከኤርትራ ውስጥ ሳህል በረሀ የተረቀቀ ሠነድ ፤ የኢትዮጵያ መፈራረስና የሕዝቧንም መበታተኛ መሰሪያ እንዲሆን መፈቀዱ፤ የዚያን

ታጋይ ትውልድ ልብ ያቆስላል!  የታሪክም ምፀት ነው። ለሀገሩ የተሻለ ዕድል ለማምጣት ሲታገል የተሰዋ ትውልድ ፤ ከናድያው (?)፤ ኢትዮጵያ በሞትና -ሽረት መካከል ሆና ሲያያት፤ ልቡ ይደማል።

" በበልግ ወራት ያላረሰ ገበሬ ፤ በአዝመራ ወቅት ይለምናል ። " እንደሚባለው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም፤ እንዲሁ፤ እስካሁን ድረስ፤ በትግሉ ሂደት ሁነኛ ድሉን ሳያዘጋጅ እየቀረ፤ ነፃነቱን ከነጠቀው ኃይል ነፃነቱን እየለመነ ይገኛል። ማንም ሕዝብ ፤ የተነጠቀውን ነፃነት ፤ ከነጣቂው እጅ አገኛለሁ ብሎ መጠበቅ ፤ከጅልም ጅልነት ነው። ለዚኽም ነው ፤ ያ **ሀገር** ወዳድ ዐብዮታዊ ትውልድ የትግልን አስፈላጊነት አምኖ፤ ጨክኖ ለመታገል የቆረጠው ። የቀጠለው ።

ይኸ ሀቅ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ትግሉ ዒላማውን ሳይመታ በመዘገየቱ፤ ያ ባላደራ ትውልድ ፤ቁጭቱን አንግቦ፤ ንዴቱን አርቆ ፤ብስጭቱን አለዝቦ ፤ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ በአምክንዮ እየገመገመ ፤ ዝናሩን ሳያላላ ለመቀጠል የወሰነው ! የሕዝብ ፍቅርና የትግል ቃል-ኪዳን የማይነጣጠሉ በመሆናቸው ነው። ሁለቱን ፤ ተሸክሞ መጓዝ ቀላል አንዳልሆነ የሚያውቀው ያውቀዋል። የታለመለት ዐላማ ግቡን ሳይመታ መዘግየቱ፤ የአዕምሮ ቁስል ፤ የኅሊና ዕርፍት ማጣትና ፤ የዘወትር ራስ ምታት ሆኖበታል ።

ለሀገር አንድነትና ለሕዝብ ነፃነት ሲል የሚታገለው ትውልድ የቆመው ፤ለይስሙላ ትግል ባለመሆኑ፤ ሁለት ታላላቅ ኃላፊነት አንግቦ ይጓዛል ። <u>አንደኛው</u> ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባው ቃል-ኪዳን ሲሆን፤ <u>ሁለተኛው</u> ደግሞ ፤የሰማዕታት ጓዶቹን አደራ የመጠበቅ ኃላፊነት ስለአለበት ነው ። እነኝኽ ጥንድ ኃላፊነቶችን አንግቦ፤ ማብቂያው ያለየለትን ትግል ማካሄድ ተስፋ አስቆራጭ መስሎ ሊታይ ይችል ይሆናል። ቃል- ኪዳንን ጠብቆና አደራን ተሸክሞ መታገል የየራሱ የሆነ ተፅዕኖ ሊኖረው ቢችልም፤ ሁሉንም እንደ አመጣጣቸው እያስተናገዱ መጓዝ፤ የትግል ተመክሮ ውጤት ነው። ። ያም ሆኖ ፤ የሰማዕታቱ ትግል የታሰበውን ውጤት ያለማስመዝገቡ ጉዳይ እንደ ዕግር ዕሳት እያንገበገበው ይገኛል።

ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት የተሰውት ፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ብልፅግና ፤ ለሠላምና አብሮ መኖር ሲሆን ፤ ዛሬ፤ ዜጎቿ በብሄርና በቋንቋ፤ በሃይማኖት እንዲከፋፈሉ በመደረጉ፤ የሠማዕታቱ አፅም ዕረፍት አላገኘም። የሀገሪቱ ቆዳ ስፋት ተጨረማምቶ የባህር ወደብ እንዳታገኝ በመደረጉ፤ ያ ከባድ ዋጋ ያስከፈለው ትግል መና እንደሆነ ተቆጥሯል። ይኸ ራሱን የቻለ አንገብጋቢ ዕረፍት ነሺ ሀገራዊ ሸክም ሆኗል ። ዜጎቿ በስብዕነታቸው ብቻ በየትኛውም የሀገራቸው ክፍል በብሄር ሳይሆን በዜግነታቸው ብቻ ተደራጅተው የሚታገሉት ኢትዮጵያውያን እንደ ሃጢአተኞችና ምፃዐተኞች ተቆጥረው፤ ልክ እንደ ባዕድ ዜጎች እየተፈናቀሉ ማየት፤ ኅሊናን ያደማል ።ይኸ ደግሞ፤

ትግሉን ለቀጠለው ትውልድ የሞት ሞት ሆኖበታል። ሞትን በሞት ሽሮ ነጻነትን ከመጎናፀፍ በስተቀር ፤ ሌላ ምርጫ እንደሌለ መረዳት ለትግል ከፍተኛ ግብዓት አለው።

ሞትን በሞት መሻር ሲባል፤ መገዳደል እንደሚኖር መገንዘብ ከባድ አይደለም ። በተለየም፤ የአንድን ሀገር ዜጎች ወደማያባራ ደም ማፍሰስ የሚያስገባ አስገዳጅ ሁኔታ ፤ ማቆም ነበረበት ። ግን ቀጥሏል። ለሀገሪቱ የተሻለ ዕድል ለማስገኘት፤ሁሉም ሊያስብበት ይገባል። ሠላምን እየሰበኩ ፅንፈኞቹን ለጦርነት ማዘጋጀት ፤ በሁለት ካራ መብላት ነው። " መሀል ሰፋሪ በሁለት ጥይት ይመታል" እንደሚባለው በሁለቱ በኩል የሚተኮሰው ጥይት ማንንም አይምርም።

ለአለፉት ግማሽ ምዕተ-ዐመት፤ የኢትዮጵያውያኑ ደም እንደ ጎርፍ ፈስሷል። ደም ማፍሰስ ፤ደም ማፍሰስን የሚያስከትል መሆኑን ያልተረዱ ሁሉ፤ ወደ ሥልጣን በሚመጡበት ጊዜ፤ በሥልጣን ለመቆየት በሕዝብ ደም እጃቸውን ከማጠብ በቀር፤ ሌላው አማራጭ ሁሉ ይዘጋባቸዋል። ወያኔዎች ፤ የእርስ በእርስ ደም መፋሰስን የሚያካሂዱት፤ ከታሪክ ያለመማር ችግር ሆኖባቸው ነው። የታሪክ ምፀት በሀገራችን መደጋገሙን ቀጥሏል;። ትላንት በደርግ ዘመን የፈሰሰው የኢትዮጵያውያን ንፁህ ደም ይበቃ ነበር። የሀገራችን የመከራ ፅዋ ሞልቶ ከፈሰሰ ዘመናት አልፈዋል። ሕዝቡ የሚመኘው ሠላምንና ብልፅግናን እንጅ፤ ደም መፋሰስንና መከራን፤ ስደትንና መፈናቀልን አይደለም። የታሪክን ሮሮ መስታወስ ቢቻል ኖሮ፤

" ጠላት ያፈሰሰው የኢትዮጵያውያን ደም ፤

መተማ ደረቀ በዮሀንስ አፅም "

ተብሎ የተሰማው እንጉርጎሮ በበቃ ነበር ! የዛሪዎቹ የዐደዋ ተወላጆች ግን፤ ይኽንን ታሪካዊ መልዕክት ትቢያ እንዲለብስ አድርገውታል። ከትቢያ አንስቶ የሕዝቡን እንባ ለማድረቅ ትግሉን የቀጠለው ያ ባለቃል -ኪዳን ትውልድ ፤ ዐላማን ሳይስት፤ ግንባሩን ሳያጥፍ ፤ ዘምሩልኝ፤ አልቅሱልኝ ሳይል፤ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊት ሀገር እስክትሆን ድረስ ትግሉን ይቀጥላል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !